# መጽሐፍ ቅዱስ ለህፃናት
## አቅራቢዎች

# የኢየሱስ ተአምራቶች



ጸሐፊው: Edward Hughes
የተተረጎመው: Eyerusalem Dechasa
ምሣሌ አቅራቢው: Byron Unger; Lazarus
ያሻሸለው (አሻሽሎ የጻፈው): E. Frischbutter; Sarah S.

ታሪክ 40 ከ 60 ዎቹ መሃከል

www.M1914.org

***Bible for Children,*** *PO Box 3, Winnipeg, MB R3C 2G1 Canada*

ፈቃድ፡- ይህንን የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ማባዛት ወይም ማተም ይቻላል
ነገር ግን ይህ መሆን የሚችለው ለሽያጭ ካላቀረባችሁ ብቻ ነው።

አማርኛ

Amharic

ኢየሱስ በርካታ ተዓምራቶችን አድርጎ ነበር። ተአምራት ኢየሱስ በእርግጥ የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን የሚያሳዩ ምልክቶች ናቸው።



1

የመጀመሪያው ተአምር በአንድ የሠርግ ድግስ ላይ ተከስቶ ነበር። በሰርጉ ላይ ችግር ተከሰተ። ለሁሉም ሰው የሚሆን በቂ ወይን አልነበረም።



2


የኢየሱስ እናት, ማርያም ስለተፈጠረው ችግር ነገረችው። ከዚያም ለአገልጋዮቹ ኢየሱስ የሚላቸውን ሁሉ እንዲያደርጉ ነገረቻቸው።
3
ኢየሱስም "ጋኖቹን ውኃ ሙሉአቸው" አላቸው። "ውሃ?" ብለው ይጠይቁ ይሆናል። አዎን, ኢየሱስ ያዘዘው ውኃ ነው።
4
ኢየሱስም ለአገልጋዮቹ ውሃ ከተሞሉት ከትልቁ ጋን ቀድተው ለባለድግሱ እንዲያቀምሱት አዘዛቸው። ውኃው አሁን ወይን ነበር! ጥሩ ወይን! ምርጥ ወይን!
5
አገልጋዮቹ ተደነቁ። ምክንያቱም ኢየሱስ ውኃውን ወደ ወይን ለውጦታል። እንዲህ ያለውን ተአምራት ሊያደርግ የሚችለው እግዚአብሔር ብቻ ነው።
6
ኢየሱስ ሌሎች ተዓምራቶችን ማድረግ ጀመረ። በአንድ ምሽት እሱና ደቀመዛሙርቱ ወደ የጴጥሮስ ቤት አቀኑ። የጴጥሮስ አማት በከባድ ትኩሳት ታማ ነበር።
7
ኢየሱስ የታመመችውን ሴት እጅ ዳሰሰ። በዛው ቅፅበት ተፈወሰች። እሷም ኢየሱስንና ደቀ መዛሙርትን ለማገልገል ተነሳች።
8


በዚያም ምሽት የከተማው ሰዎች
በበሩ ጋር ተሰበሰቡ። የታመሙ
ሰዎችም መጡ - ዓይነ
ስውሮች, ደንቆሮዎች,
ዲዳዎች, ሽባዎች።
በአጋንንት እስራት
ውስጥ ያሉ ሰዎችም
እንኳ ሳይቀሩ ወደ
ኢየሱስ ይጎርፉ
ነበር። ይህ ሁሉ
ሰው ይረዳ ይሆን?
9


አዎ! ኢየሱስ, የእግዚአብሔር ልጅ ሊረዳቸው ይችላል። ኢየሱስ
ረድቷቸውም ነበር። በህይወታቸው ሁሉ በምርኩዝ ሲጓዙ የነበሩ
ሰዎች መራመድ ፣ መሮጥ እና መዝለል ቻሉ።
10


ሌሎችም በሥጋ
ደዌ የታመሙ
ሰዎች መጡ።
11


ኢየሱስም
ሲፈውሳቸው
ሙሉና ንጹህ
ሰዎች ሆኑ።
12


በአጋንንት የተጨነቁ
ወንዶች እና ሴቶች
በኢየሱስ ፊት
ቆሙ። ኢየሱስም
ሰይጣኖቹን ከነሱ
እንዲወጡ
አዘዛቸው።
አጋንንቶቹም
ሲታዘዙ አስፈሪ
እና ደስተኛ
ያልሆኑት ሰዎች
የተረጋጉ እና
ደስተኞች ሆኑ።
13


ከሕዝቡ በስተጀርባ አራት ሰዎች የታመመ ወዳጃቸውን ይዘው
ወደ ኢየሱስ መጡ። ነገር ግን ወደ እርሱ መቅረብ አልቻሉም።
ምን ያደርጉ ይሆን?
14



የታመመውን ሰውተሸክመው በቤቱ ጣሪያ ላይ ወጡ። አራቱ ታማኝ ጓደኞቹ ጣራውን ቀደው ወደ ታች አወረዱት። አሁን ወደ ኢየሱስ በደንብ ቀረበ።

15

ኢየሱስ እነዚህ አራት ጓደኞች እምነት እንዳላቸው ተመለከተ። የታመመውን ሰው "ኃጢአትህ ተሰረየልህ; መኝታህን አንሳና ሂድ" አለው። ሰውየውጠንካራ ሆኖ ተነሳ። ኢየሱስም ፈወሰው።



16



ከጥቂት ጊዜ በኋላ ኢየሱስ ከደቀ መዛሙርቱ ጋር በጀልባ ተሳፍሮ ነበር። ኃይለኛ አውሎ ነፋስ በባሕሩ ላይ ሆነ። ኢየሱስ ግን ተኝቶ ነበር። የተረበሹት ደቀ መዛሙርት ኢየሱስን ከእንቅልፉ ቀሰቀሱት። "ጌታ ሆይ, አድነን መጥፋታችን ነው" ብለው ጮኹ።

17

ኢየሱስም ማዕበሉን "ፀጥ በል!" ብሎ አዘዘው። ወዲያውም ባሕሩ ጸጥ አለ። ደቀመዛሙርቱም "ይሄ ምን ዓይነት ሰው ነው?" ብለው አንሾካሾኩ። ነፋስና ባሕር እንኳን ይታዘዙለታል እነርሱም ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ ነው ብለው አመኑ ምክንያቱም ተዓምራቶቹ ክብሩን ያሳያሉና።



18

የኢየሱስ ተአምራቶች

ይህ ታሪክ የሚገኘው የእግዚአብሔር ቃል በሆነው መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ

ማቴዎስ 8-9፣ ማርቆስ 1-2፣ ማርቆስ 4፣ ሉቃስ 4፣ ሉቃስ 8፣ ዮሐንስ 2

“የቃልህ ፍቺ ያበራል.”
መዝሙረ ዳዊት 119:130

ክፉ ነገሮችን እንዳደረግን እግዚአብሔር ያውቃል፣ ኃጢአት ብሎም ይጠራዋል።

እግዚአብሔር እጅግ በጣም ስለወደደን አንድያ ልጁን ለመስቀል ሞት አሣልፎ በመስጠት የኃጢአትን ዋጋ በሞቱ ከፍሎልናል። ኢየሱስ ህያው ሆኖ ከሞት መነሣት ወደ ሠማይ አርጓል። አሁን እግዚአብሔር ኃጢአታችንን ይቅር ይለዋል።

ከኃጢአታችሁ ለመመለስ ከወሰናችሁ ለእግዚአብሔር እንዲህ በሉት። እግዚአብሔር አምላክ ሆይ ኢየሱስ ክርስቶስ ለእኔ ኃጢአት ሲል እንደሞተና አሁን ህያው ሆኖ እንዳለ አምናለሁ። እባክህ ወደ ህይወቴ ግባና ኃጢአቴን ሁሉ ይቅር በል ስለዚህ አዲስ ህይወት ይኖረኛል ደግሞ ከአንተ ጋር ለዘላለም እኖራለሁ። ጌታ ሆይ እንደ ልጅ ለአንተ እንድኖርልህ እርዳኝ አሜን። ዮሐ. 3.16